# ስለ ወደፊቱ አዲስ ሕዝባዊ ሕብረት አመሰራረት የምለው አለኝ

<u>የትኛው ሕብረት?</u>

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ድርጅቶች ባንድ ተሰባስበው የጋራ የሆነውን ጠላታቸውን ለመፋለም የሚፈጥሩት ጥላ ድርጅት ግንባር፣ ሕብረት፣ስብስብ ወይም ቅንጅት ተብሎ ሊጠራ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ:: ሁሉም ተመሳሳይ ትርጉም ቢኖራቸውም የተለመደውን ሕብረት የሚለውን ስያሜ እንምረጥ :: ሁለት አይነት ሕብረት ሊኖሩ እንደሚችሉም እገነዘባለሁ፡ሕዝባዊና ጸረ-ሕዝባዊ:: ጸረ-ሕዝባዊ የሆኑ በእንደ ኢሕአዴግ አይነቱ ይገለጻሉ::ፀረ-ሕዝባዊውን ሕብረት ያለችግር መረዳት የሚቻል ነው:: ሕዝባዊ ነው ያልነውም ሕብረት ስሙ ሕዝባዊ ስለሆነ ብቻ ሁሉም ሕዝባዊ ነው ከሚል ፈጣን ድምደማ ከደረስን ደግሞ ሕዝቡን ሲክዱ ሥናይ ምን እንደምንላቸው እንዳይጨንቀን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል:: ከተመክሮ አይተናል:: ተምረናልም::

ዛሬም እንደትናንቱ ኢትዮጵያችን በታላቅ ቀውስ ውስጥ ናት:: ሕዝቧም እጅግ ከፋፋይና ጨቋኝ በሆነ እጥፊ መንግስት ስር ወድቋል:: ከዚህ ቀውስ ለመውጣት ያንድ ሕዝባዊ ድርጅት አቅም ብቻ በቂ ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው:: ለዚህም ነው ድርጅቶች ባንድ ሕዝባዊ ሕብረት ስር መሰባሰብና መታገል አለባቸው የሚባለው:: "<u>ድር ቢያብር አንበሳ ያስር</u>" የሚለው ያበው አባባል መልዕክተ በጣም ጠቃሚ ይሆናል:

<u>ሕዝባዊ ሕብረት ለምን?</u>

ጠላትን በተባበረ ኃይል መዋጋት በኢትዮጵያ የቅርብና የሩቅ ታርኳ ውስጥ የታየ ሃቅ ነው:: አሁንም ሕዝባዊ ሕብረትን መፍጠር የግድ የሚል ወቅት ላይ ነን ያለነው:: በጠላትነት በላያችን የሰፈነው ወያኔ ተግባራቱ አስከፊና እልህ አስጨራሽ ናቸው:: እስካፊንጫውም የታጠቀ ነው:: አስከፊ ተግባራቱና መጠን የሌለው መሳሪያው በቀላሉ የማይሰበር ኃይል አጎናጽፈውታል:: በተለይም ደግሞ የሕዝባዊው ክፍል ኃይሉን ባንድ ሕብረት ስር መሰብሰብ ባለመቻሉ ያለውን የወያኔ ኃይል የበለጠ ያሳብጥለታል::

ባጭሩ የተበታተኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች ኃይላቸውከወያኔ ሰራዊት ጋር ሊመጣጠን ስለማይችል በተናጠል የሚያደርጉት ትግል የማያዋጣና ብሎም ተራ በተራ ለገዥው ኃይል የሰለባ ሲሳይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል:: ያልተቀናጀ ትግላቸውም ሕዝቡን ያስመታል::

<u>ሕዛባዊ ሕብረትን ለመፍጠር መስፈርቶቹ ምንድናቸው?</u>

1. በቅድሚያ ሕዝባዊ ሕብረትን የሚመሰርቱ ድርጅቶችበኢትዮጵያ ልዑላይነት የሚያምኑና በተግባርም የሚተረጉሙ ሊሆኑ ይጠበቅባቸዋል: "መገንጠል ወይም ሞት" ከሚሉ ድርጅቶች ጋር የሚፈጠር በኢትዮጵያ አንድነት ላይ የሚያምን ሕዝባዊ ሕብረት ከቶውንም ሊኖር አይችልም:: ሕብረትን ስለሕብረት ብለው የሚቀላቀሉ ድርጅቶች ከውዲሁ እንኳንየኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻ ሊያወጡ ቀርተው የራሳቸው ህልውና ከጠላት ወያኔ ማስጠበቃቸው ህልም ነው::ሕዝባዊ የሆኑትን ድርጅቶች አግልሎ ባላማና በፓለቲካ ፕሮግራማቸው የምድርና የሰማይ ያህል ከተራራቀ ድርጅቶች ጋር ግንባር ለመፍጠር ሽር ጉዱ ሳይውል ሳያድር የለቅሶ መድረክ ነው የሚሆነው::

2. በጋራ ጠላት ላይ ከስምምነት ላይ መድረስ ወሳኝ ነው:: እዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ አለ: የጋር ጠላት ያላቸው ሁሉ አንድ አቋም ይይዛሉ ብሎ መደምደም አይቻልም: በሌላ አነጋገር የወያኔ ጠላት የሆነ ሁሉ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ወዳጅ ነው ብሎ መደምደሙ የዋህነት ያለያም ቂልነት ነው፡እውነተኛ

ምሳሌ እናንሳ፡፡ ወያኔ ለኢትዮጵያና ለሻቢያ ጨላት ነው፡፡ ኢትዮጵያና ሻቢያ የጋራ ጠላት(ወያኔ) ስላላቸው ወዳጅ ናቸው ብሎ መደምደም ስህተት ነው፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያና ሻቢያ(የአርትራ ሕዝብ አላልኩም)ወዳጅም ሆነው አያውቁም፡፡ባጭሩ ተመሳሳይ የጋር ጠላት ስላለ ብቻ ሕዝባዊ ሕብረት ለመመስረት በቂ መመዘኛ ሊሆን አይገባውም፡ የኢትዮጵያና የሕዝቧ ጠላት የሆነ ኃይል(ድርጅት) የመረረ የወያኔ ጠላት ስለሆነ ብቻ የኢትዮጵያና የሕዝቧ የቁርጥ ቀን ወዷጅ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር በሕዝባዊው ሕብረት ሊካተት አይሞከርም፡፡እንደ AFD አይነቱን የኢትዮጵያን ጠላቶችና ወዳጆች ያቀፈ ስብስብ ሳይወለድየሞተው እኮ ለዚሁ ነው፡፡

3. በሕዝባዊው ሕብረት ስር የሚሰባሰቡ ድርጅቶች ብቃት ያላቸውሊሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከፖለቲካ ፕሮግራማቸው ባሻገር ድርጅታቸው ሊነክስ የሚችል ጥርስ ሊኖረውም ይገባል፡ እንደ ድስት ጉልቻ ሶስት አባላት ብቻ ያሉት ሳይሆን በቂ የሆነና ከሕዝብ መሃል በሕቡዕም ይሁን በግልጽ ስር የሰደደ ያባላት ብዛት ያለው መሆን አለበት፡፡ "አሻሮ ይዞህ ከቆሎ ተጠጋ" አይነት መሆን የለበትም፡፡ የፈረሰውን የሕብረት ታሪክ ሁላችንም የምናስታውሰውን የቆሎና ያሻሮ ታሪክ ያለው ሕዝባዊ ሕብረት ዳግም እንዳይደገም ካሁኑ ልናስብበት ይገባናል፡፡

4. አስመሳይ ተቃዋሚ ድርጅቶች ከሕዝባዊውሕብረት እንዳይገቡ ነቅቶ ዘብ መቆም ያስፈልጋል፡፡ አስመሳይ ድርጅቶችን ቶሎ ለመለየት አስቸጋሪነቱ አያጠያይቅም፡ ቆራጥ የሕዝብ ወገን መስለው ይታያሉ፡፡ አስመሳይም የተባሉት በዚህ የላቀ ችሎታቸው ነው፡፡ ጊዜ ፈጅቶ የኋላ ኋላ ግን እንጀነ በየነ ጴጥሮስና አንደነ ልደቱ ቁልጭ ያለው መልካቸው ብቅ ማለቱ አይቀርም፡፡ መጥፎነቱ የሚነቃባቸው ሕብረቱን ቦርቡረ ቦርብረው ሊሞት አንድ ጀምበር ሲቀራቸው ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የድርጅት አሰላለፍየምናየው አብዛኛዎች አስመሳይ ተቃሚዎች መሆናቸውን ነው፡ ያዙኝ ልቀቁኝየሚሉትም እነዚሁ አስመሳይ ተቃዋሚዎች ናተው፡ የሚስፈነጠሩትም አስመሳይነታቸውን የደበቁ እየመሰላቸው ነው፡፡ የሕዝብ ወገን የሆኑትማ "ሙያ በልብ" እያሉ ሕዝቡን ለማይቀረው ድል እያዘጋጁት ይገኛሉ፡፡

5. ሕዝባዊ የሆኑት ድርጅቶች በሚያቀራርባቸው ላይ እየተግባቡ ልዩነታቸውንም እያቻቻሉ ወያኔን በመቋቋም ትግላቸውን ማጧጧፍ አለባቸው፡ ድርጅታዊ የበላይነትን ለማስፈን ወይም ተክሉሰውነትን ለማንገስ ከሚደክሙ እወቁኝ ባዮች መራቅ ከሕዝባዊ ድርጅቶች የሚጠበቅ ግዳጅ ነው፡ጠላትን ለማንበርከክ፤ አገሪቷን ከመበታተን ለመጠበቅና ሕዝቡን የስልጣኑ ባለቤት ለማድርረግ አንድ ድርጅት ለብቻው የማይወጣው ሃላፊነት መሆኑን አምኖ በሕዝባዊው ሕብረት አማካይነት በጋራ የጋራ ጠላት መዋጋት ከሕዝባዊ ድርጅቶች ብቻ ሳይሆን ከሁላችንም የሚጠበቅ ግዴታችን መሆኑን ማመን ይገባናል፡፡

ወደፊት የሚፈጥረው ሕዝባዊ ሕብረት ዓላማው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያ ከሆነ እንኳን ወያኔን ቀርቶ ባራቱም ማዕዘናት ለያጠፉን ሌት ተቀን የሚያሴሩብንም የውጭ ጠላቶችንም ድባቅ ከመምታት የሚገታን አንዳችም ምድራዊ ኃይል ሊኖር አይችልም፡፡ አዲሱ ሕዝባዊ ሕብረት ዓላማው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ከሆነ ትናንት እንደተከሰተው አይነት ይልጅ ጨዋታ "ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ" አይሆንም፡፡

ጠላቶች፤ ባንዳዎችና አፍራሽ አንጃዎች ያልተሰገሰጉበት ሕዝባዊ ሕብረት እንመስርት!

ሲራክ ከምድረ አሜሪካ፥ ሚድ ዌስት
12/31/2008